# የስብሰባ ጥሪ

## ለአሐዱ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

## የባለአክሲዮኖች 5ኛ መደበኛ እና 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፤ 367 (1) እና 370 እንዲሁም በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 19.1 እና 19.2 መሠረት የአሐዱ ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 5ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው ጥቅምት 28 ቀን 2019 ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ጀምሮ አዲስ አበባ ሲኤምሲ በሚገኘው በአዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ማዕከል ስለሚያካሒድ፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተጠቀሰው ቀን፣ሰዓት እና ቦታ በጉባዔው ላይ እንዲገኙ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል።

### 1. ማኅበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

| | |
|---|---|
| 1.1 የአክሲዮን ማኅበሩ ስም | አሐዱ፡ባንክ አ.ማ |
| 1.2. የአክሲዮን ማኅበሩ ዓይነት | የባንክ ሥራ ላይ የተሰማራ የአክሲዮን ማኅበር |
| 1.3. የአክሲዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ | 1,559,702,500 |
| 1.4. የአክሲዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 1,239,574,681 |
| 1.5 የአክሲዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር | MT/AA/3/0052593/2014 |
| 1.6. የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ | አዲስ አበባ ከተማ፣ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 08፤የቤት ቁጥር አዲስ HTTP://AHADUBANK.COM |

### 2. የባለአክሲዮኖች 5ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. እ.ኢ.አ ጥቅምት 20 ቀን 2019 ዓ/ም ድረስ የተፈጸሙ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማጽደቅ
2. በባንኩ ምሥረታ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሰነዶች አሟልተው በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኣገልግሎት ቀርበው ባለመፈረማቸው በአክሲዮን መዝገብ ሰላልገቡ ግለሰቦች በተመለከተ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አቅጣጫ መሠረት የተፈጸመን ሒደት ማጽደቅ
3. እ.ኤ.አ 2025/26 ሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ
4. እ.ኤ.አ የ2025/26 ሒሳብ ዓመት የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ
5. እ.ኤ.አ የ2026/27 ሒሳብ ዓመት የውጭ ኦዲተር መሾም እና የሥራ ዋጋ ክፍያ ማጽደቅ
6. እ.ኤ.አ የ2025/26 ሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በቀረበው የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እ.ኤ.አ የ2025/26 ከተጣራ ትርፍ ላይ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ እና እ.ኤ.አ የ2026/27 ወርሃዊ አበልን መወሰን
8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ ኮሚቴን ማቋቋም
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ማከናወን

### 3. የባለአክሲዮኖች 3ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. እ.ኢ.አ እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2019 ዓ/ም ተፈርመው ክፍያ ያልተፈጸመባቸውን አክሲዮኖች ሰለመሰረዝ
2. ጥቅምት 12 ቀን 2015 ዓ/ም በባንኩ 1ኛ አሰቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እና ኅዳር 13 ቀን 2018 ዓ/ም በባንኩ 3ኛው አሰቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩን የተከፈለ ካፒታል ወደ 5 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ የተወሰነውን ውሳኔ ሰለማሻሻል የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን

### ማሳሰቢያ

- ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ከሆነ በንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሠረት ጉባዔው ከመጀመሩ ከሦስት ቀናት በፊት ድረስ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ ማቅረብ ወይም ከመስቀል አደባባይ ወደ ቦሌ በሚወስደው መንገድ ፍላሚንጎ ሬሲቶራንት ፊት ለፊት በሚገኘው ሰንሻይን ሕንጻ 4ኛ ፎቅ የባንኩ አክሲዮን ክፍል ወይም በባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ የውክልና ቅፅ መሙላት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።
- የባንኩ ሠራተኛ ለባለአክሲዮኖች ተወካይ በመሆን በጉባዔው ላይ መሣተፍ አይችልም። አንድ ባለአክሲዮን በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው።
- በአካል በጉባዔው የምትገኙ ባለአክሲዮኖች ማንነታችሁን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም ብሔራዊ መታወቂያ ማቅረብ ይጠበቅባችኋል። ባለአክሲዮኖችን በመወከል በስብሰባዉ ላይ የምትሣተፉ ተወካዮችም የወካያችሁን እና የእናንተን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና የውክልና ሰነዱን ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ ይዛችሁ እንድትቀርቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

አሐዱ፡ ባንክ አ.ማ.
የዳይሬክተሮች ቦርድ

አሐዱ፡ባንክ
Ahadu Bank

ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation